# ደንብ

ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

*ተዛማጅ ሠነዶች፦* BLB, IQA-RA, JEA, JEA-RB, JEA-RC, JEE, JEE-RA, KLA-RA
*ኃላፊነት የሚመለከተው ጽ/ቤት፦* የትምህርት ክፍል/Division of Teaching and Learning

## የትምህርት ክፍያን መሰረት ያደረገ የተማሪ ምዝገባ

I. ዓላማ

የመኖሪያ አድራቸው ሌላ አካባቢ የሆኑ ተማሪዎችን ስለመመዝገብ በሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JEA፣ *የመኖሪያ አካባቢ፣ የትምህርት ክፍያ፣ እና ምዝገባ* እና MCPS ደንብ EA-RBJ *የተማሪዎች ምዝገባ* ድንጋጌዎችን በመከተል በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ክፍያን መሰረት ያደረገ የምዝገባ ሂደት መመስረት።

እንደ አግባቡ የትምህርት ክፍያ የሚታለፍበትን መስፈርት መለየት።

II. ትርጉም

A. *እውነተኛ የመኖሪያ አካባቢ* — ማለት የአንድ ሰው ትክክለኛ ወይም እውነተኛ የመኖሪያ አካባቢ ማለት ነው፣ ነገር ግን ለተለየ ምቾት ወይም በነጻ MCPS ትምህርት ቤት ለመግባት ተብሎ ትክክለኛ ያልሆነ እና ጊዜያዊ መኖሪያ አካባቢን እንደ እውነተኛ የመኖሪያ አድራሻ አድርጎ መጠቀምን አያካትትም። ይሁን እንጂ፣ በወቅቱ ባለው የመኖሪያ ቦታ በዘላቂነት ወይም በቋሚነት መኖር የግዴታ አስፈላጊ አይደለም። የአንድን ሰው ትክክለኛ የመኖሪያ ቦታ መወሰን በየግለሰቡ(ቧ) እርግጠኝነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

B. *ከባድ ችግር/ቀውስ* — ማለት የተማሪን የትምህርት ክፍያ ለማስተው በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ድንገተኛ፣ ያልተለመደ፣ ያልተጠበቀ እና ወላጅ/አሳዳጊ ሙሉ በሙሉ ማስረጃ ሊያቀርብበት የሚችል ከባድ ክስተት ማለት ነው። ለትምህርት ቤት አቅራቢያነት ምቾት ሲባል፣ ወይም የትምህርት ቤት ፕሮግራም ምርጫን በመፈለግ፣ ወይም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ነፃ ትምህርት ለማግኘት ዓላማ የሚደረግ ሁኔታን አያካትትም።

C. *ብቁ ተማሪ* — ማለት ተማሪው(ዋ)፣ የአሜሪካ ዜጋም ቢሆን ወይም የአሜሪካ ዜግነት የሌለው/የሌላት፣ ለአካለ መጠን የደረሰ(ች) እድሜ (18) ወይም ከ18 ዓመት እድሜ በፊት ከወላጆች ተነጥሎ(ላ) የወጣ(ች)፣ በተያዘው የትምህርት አመት ትምህርት በተጀመረበት ቀን እድሜው(ዋ) ከ 20 ዓመት በላይ ያልሆነ(ች) ተማሪ ማለት ነው።

D. *በማጭበርበር መመዝገብ* — ማለት መኖርያን በሚመለከት ሆን ተብሎ የተሳሳተ የሰነድ መረጃ ማቅረብ ወይም ትክክለኛ የመኖሪያ አካባቢን ከለወጡ በኋላ 30 ቀናት ውስጥ የተደረገውን የመኖሪያ አድራሻ ለውጥ ለ MCPS አለማሳወቅ ማለት ነው።

III. *የትምህርት ክፍያን መሠረት ያደረገ የምዝገባ ሂደት*

A. *የተማሪዎች ምዝገባ* MCPS ደንብ JEA-RB *መሠረት መስፈርቱን የማያሟሉ* እና በ MCPS የትምህርት ክፍያ ድንጋጌ መሰረት ተማሪን ወይም ራሳቸውን ማስመዝገብ የሚፈልጉ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች/ብቁ ተማሪዎች በክፍያ ለመማር የተማሪ ምዝገባ ቅጽ MCPS ቅጽ 335-73A ወደ አለምአቀፍ የተማሪዎች ምዝገባ እና መቀበያ (IAE) ቢሮ *ማቅረብ አለባቸው።*

1. ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው፣ ወይም ብቁ ተማሪዎች፣ የተወሰነ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ ሊጠይቁ ይችላሉ፣ ነገር ግን MCPS ጥያቄውን የማጽደቅ ወይም ውድቅ የማድረግ መብቱ የተጠበቀ ነው፥ ወይም ለተማሪው(ዋ) የትምህርት ፕሮግራም ተስማሚ የሆኑ ኮርሶችን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚሰጥ አማራጭ ትምህርት ቤት/ፕሮግርም ላይ እንዲመዘገቡ መመሪያ የመስጠት መብት አለው። የአንድ ቤተሰብ የትምህርት ክፍያን ለመክፈል ያለው ፍላጎት በሚፈልጉት ትምህርት ቤት ወይም በመረጡት መርሐ ግብር ላይ ለመመደብ ዋስትናን አያረጋግጥም።

2. ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ምዝገባ በሚከተለው ሁኔታ ሊሆን ይችላል፡-

   a) ምዝገባው የሚፈቀደው ተማሪው(ዋ) በዚያ ትምህርት ቤት የሚሰጡትን ትምህርቶች እንዲያጠናቅቅ/እንድታጠናቅቅ ለማስቻል ብቻ ከሆነ፥ ተማሪው(ዋ) ወደ ቀጣዩ የትምህርት ደረጃ (አንደኛ ደረጃ ት/ቤት፣ መካከለኛ ደረጃ ት/ቤት ወይም ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ለመግባት እንደገና ማመልከት አለባቸው።

   b) MCPS ደንብ JEE-RA *የተማሪ ዝውውር እና አስተዳደራዊ ምደባዎች* ደንብ ላይ በተገለጸው መሰረት ርእሰመምህር ተገቢ በሆነ ምክንያት IAE ነዋሪ ያልሆነ(ች)ን ተማሪ ምዝገባ እንዲሰርዝ ሊጠይቅ ይችላል።

   c) በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለመመዝገብ የሚፈልጉ ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በሚደረግ የአትሌቲክስ ውድድር ለመግባት አዲስ በተመዘገቡበት ትምህርት ቤት ውስጥ አንድ አመት መማር አለባቸው።

      1) ቤተሰቦቻቸው ነዋሪነታቸውን ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ከለቀቁ በኋላ በክፍያ ትምህርታቸውን ለሚቀጥሉ ተማሪዎች ይህ በኢንተር-ስኮላስቲክ አትሌቲክስ ውስጥ የመሳተፍ እገዳ በእነርሱ ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን ይደረጋል።

      2) ነዋሪ ያልሆኑ በመካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የትምህርት ክፍያ እየከፈሉ የሚማሩ ተማሪዎች ወደ ተመሳሳይ መጋቢ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገቡ ከሆነ የአንድ አመት ገደብ እገዳ አይመለከታቸውም።

      3) ነዋሪ ላልሆኑ ተማሪዎች በ IAE ዲሬክተር ውሳኔ ተመዝግበው ባጋጠማቸው ቀውስ ምክንያት የትምህርት ክፍያ ቀርቶላቸው እንዲማሩ የተፈቀደላቸው ተማሪዎች በኢንተር-ስኮላስቲክ አትሌቲክስ ውስጥ ለመሣተፍ የአንድ አመት ገደብ አይጣልባቸውም።

   d) ተማሪዎች ባመለከቱባቸው ፕሮግራሞች ምክንያት ብቁ ሊሆኑ አይችሉም (ለምሳሌ፡- የቋንቋ ኢምርዥን፣ ማግኔት፣ ኢዲሰን)።

3. MCPS ቅጽ 335-73A ተሞልቶ የቀረበውን IAE ከገመገመ በኋላ፣ ከተጠየቀው ትምህርት ቤት ርእሰ መምህር/ተወካይ ጋር እንዲሁም ከሌሎች ት/ቤቶች ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ጋር ከተመካከረ በኋላ በሚከተሉት ቅድመ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ውሳኔ ይሰጣል።

   a) ተጨማሪ ተማሪዎችን ለማስተናገድ ክፍል ውስጥ፣ በትምህርት ቤቱ፣ እና በክላስተሩ በቂ ቦታ/አቅም መኖሩን ማረጋገጥ --

      1) በወቅቱ ለክፍሉ፣ ለትምህርት ቤቱ፣ እና ለክላስተሩ የታለመ እና የታቀደ የምዝገባ መጠን፣

      2) የህንጻውን አጠቃቀም እና የክፍል ተማሪዎችን መጠን መመሪያዎች ማገናዘብ፣ እና

      3) የሰው ኃይል ምደባ ግምት ውስጥ መግባት አለበት።

   b) ትምህርት ቤቱ ለተማሪው የትምህርት ፕሮግራም ፍላጎት ተስማሚ የሆኑ ኮርሶችን እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን መስጠት እንደሚችል።

   c) የተጠየቀው ትምህርት ቤት ወይም አማራጭ ትምህርት ቤት በጥያቄው ውስጥ ለተገለጸው ልዩ ችግር ምላሽ መስጠት መቻሉን።

   d) ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎች ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ተማሪዎች ጋር በመወዳደር በጣም ተፈላጊ ኮርሶችን ወይም ፕሮግራሞችን ምርጫ ማግኘት አይችሉ ይሆናል።

B. ከላይ የተጠቀሱትን ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ቅጽ 335-73 ላይ ከተጠየቀው ትምህርት ቤት ውጪ IAE ሌላ ትምህርት ቤት እንዲሞከር የመምከር መብቱ የተጠበቀ ነው።

C. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ማሳደጊያ ወይም በቡድን መኖሪያ ቤት ተማሪዎችን የሚያስገቡ ከስቴት ውጪ ያሉ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች MCPS ቅጽ 335-73፣ *የነዋሪነት እና የትምህርት ክፍያ ሁኔታ ውሳኔ ቅጽ* ለ IAE ማቅረብ አለባቸው።

   1. ከስቴት ውጭ በሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ አማካይነት የተመደቡ ተማሪዎች IAE ከትምህርት ቤት አመራር እና ማሻሻያ እና የተማሪ ድጋፍ እና ክትትል አገልግሎት ክፍል ጋር በመመካከር በሌላ ሁኔታ እንዲታይ ካልወሰነ በስተቀር በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ በሚገኝ የልጆች ማሳደጊያ ወይም የቡድን መኖሪያ ቤት አድራሻ ትምህርት ቤት ተመድበው የትምህርት ክፍያ ሊሠረዝላቸው ይችላል።

   2. የዲስትሪክት ኦቭ ኮሎምቢያ የህጻናት እና ቤተሰብ አገልግሎት ኤጀንሲ (DC-CFSA) ነዋሪ ላልሆነ ተማሪ ክፍያ ይጠየቃሉ፣ እና MCPS ቅጽ 335-73፣ *የነዋሪነት እና የትምህርት ሁኔታ ውሳኔ*እና MCPS ቅጽ 335-73A፣ *ነዋሪ ያልሆኑ ተማሪዎችን ትምህርት ቤት ማስገቢያ ጥያቄ* ማቅረብ አለባቸው።

C. ስለ ትምህርት ክፍያ በየዓመቱ በቦርድ ይወሰናል።

D. የሙሉ ክፍያ ተመን የዕዳ ቅነሳ አገልግሎትን ጨምሮ ለተማሪ ከሚወጣው አማካይ ወጪዎች ጋር

ተመጣጣኝ ይሆናል፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን በእያንዳንዱ ክፍል ደረጃ ተማሪዎችን የማስተማር ትክክለኛ ወጪን የሚያንፀባርቅ ይሆናል።

E. የልዩ ትምህርት አገልግሎት ለሚያገኙ አካል ጉዳተኛ ተማሪዎች፣ የዕዳ ክፍያ አገልግሎትን ጨምሮ ተጓዳኝ አገልግሎቶችን ለመስጠት በተገመተው ወጪ መጠን መደበኛውን የሙሉ ዓመት ክፍያ ያንፀባርቃል።

F. ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ውጪ ለሚኖሩ የ MCPS ሠራተኞች ልጆች የሙሉ ጊዜ የትምህርት ዓመት ክፍያ መጠን እና/ወይም የሰመር ስኩል ክፍያ አንድ አይነት የክፍል ደረጃ ላይ ያሉ እና ተመሣሣይ አገልግሎት ከሚያገኙ ከሌሎች በካውንቲው ነዋሪ ካልሆኑ ተማሪዎች የክፍያ መጠን ግማሽ ይሆናል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች በትምህርት ዓመቱ በሙሉ ከደሞዛቸው ፔይሮል ተቆራጭ እየተደረገ እንዲከፈል ወይም አመታዊ የትምህርት ክፍያውን በሙሉ ከትምህርት አመቱ መጀመሪያ በፊት መከፈል አለባቸው።

G. የትምህርት ክፍያዎች

1. III.H.1 ወይም III.H.3. ውስጥ ከዚህ በታች ባሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር፣ ተመዝግበው በትምህርት ላይ ያሉትም ሆኑ ወይም ለቀው የወጡበት ቀን ምንም ይሁን ምን ተማሪዎች ለተመዘገቡበት ሴሚስተር ሙሉ የትምህርት ክፍያ መክፈል አለባቸው።

2. የትምህርት ክፍያ ዋጋን በተመለከተ ከ IAE ወይም ከፋይናንሺያል ማኔጅመንት ተቆጣጣሪ ክፍል መረጃ ሊገኝ ይችላል።

3. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቀጣሪ ላልሆኑ ሰራተኞች ክፍያው በየሴሚስተሩም ሆነ በአመት ይፈፀማል። የመጀመሪያው ሴሚስተር የትምህርት ክፍያ ኦገስት 1 ይፈጸማል እና ለሁለተኛው ሴሚስተር የትምህርት ክፍያ ከዲሴምበር 31 በፊት ይፈጸማል።

4. የትምህርት ክፍያዎች በወቅቱ ካልተፈጸሙ፣ ባልተከፈለው ቀሪ ሂሳብ ላይ በወር 1 በመቶ/ፐርሰንት ወለድ ይጨመራል። የትምህርት ክፍያን አለመክፈል፦ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት ማንኛውም ያልተከፈለ ዕዳ ወደ ክፍያዎች ሰብሳቢ ኤጀንሲ እንዲተላለፉ እና ተማሪው(ዋ) ከ MCPS እንዲወጣ ሊያስደርግ ይችላል።

    a. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተቆጣጣሪ ክፍል IAE ለቤተሰቡ እንዲያሳውቅ ያደርጋል።

    b. IAE ማስታወቂያ ከሰጠ ሰባት ቀናት ውስጥ ተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቤት ይሰረዛል/ትሠረዛለች፣ እና ማንኛውም ያልተከፈለ ክፍያ ወደ ክፍያ ሰብሳቢ ኤጀንሲ ሊተላለፍ ይችላል።

5. ተማሪ በማጭበርበር መመዝገቡ ከተረጋገጠ ከ MCPS ይወጣል/ትወጣለች። ወላጅ(ወላጆች)/አሳዳጊ(ዎች) ለተጭበረበረ ምዝገባ ወይም ለተማረ(ች)በት ወቅት የትምህርት ክፍያ ገንዘብ ተጠያቂ ይሆናሉ።

6. F-1 ቪዛ ያላቸው ተማሪዎች MCPS ደንብ JEA-RC፣ *የአለም አቀፍ እና የውጭ ተማሪዎች ምዝገባ እና ምደባ* መሰረት ትምህርት ከመጀመራቸው በፊት ክፍያ መፈፀም ይጠበቅባቸዋል።

H. ተመላሽ ክፍያ እና በተመዛዛኝ ክፍያ

1. በተመዛዛኝ የትምህርት ክፍያ ወይም በተመዛዛኝ ተመላሽ ክፍያዎች ሊፈጸሙ የሚችሉት በሚከተሉት ምክንያቶች ብቻ ነው፦

   a) ተማሪው(ዋ) ነዋሪ መሆኑ(ኗ)ን ታሳቢ በማድረግ ወይም IV.C ክፍያ እንዲሠረዝለት/እንዲሠረዝላት ባለሙብት የሆነ(ች) ለማናኛውም ያክል ጊዜ በቅድሚያ የተደረገ የትምህርት ክፍያ፣ ወይም

   b) ተማሪው(ዋ) ትምህርት ቤት በሚመዘገብበት/በምትመዘገብበት ወቅት ነዋሪ ከነበረ(ች) እና በኋላ ላይ ነዋሪነት ከለቀቀ(ች) እና ከካውንቲው ውጪ እየኖረ(ች) በክፍያ ለመመዝገብ ከጠየቀ(ች)፣ ወይም

   c) ተማሪው(ዋ) ከስቴት ውጭ በሆነ የማህበራዊ አገልግሎት ኤጀንሲ ወደ MCPS ሲመደብ እና ከትምህርት መጀመሪያ ቀን በኋላ ከተመዘገበ(ች) እና/ወይም ከሴሚስተሩ የመጨረሻው የትምህርት ቀን በፊት ከትምህርት ቤት ከለቀቀ(ች)።

2. III.H.1 በተገጸው የክፍያ ምጥጥን መሠረት የዓመቱን የትምህርት ክፍያ መጠን በትምህርት ቀኖች ብዛት እየተካፈለ በእያንዳንዱ የትምህርት ቀን ሂሳብ መጠን ይሠላል፣ ከዚያም ተማሪው(ዋ) በተማረ(ች)ባቸው ቀኖች እየተባዛ የክፍያ ምጥጥን/prorated ይደረጋል።

   a) የትምህርት ክፍያ ገንዘብ ተመላሽ ለማድረግ ስሌት የሚደረገው ተማሪው(ዋ) በይፋ ከትምህርት ቤት የተሰናበተ(ች)በትን ቀን ተሞርኩዞ ነው።

   b) ተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቤት እስከሚለቅበት/እስከምትለቅበት ቀን ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ፣ ተማሪው(ዋ) ከትምህርት ቤት ለቀረ(ች)ባቸው ቀናት ምንም አይነት የትምህርት ክፍያ ተመላሽ አይደረግም።

3. ርእሰመምህር/ተወካይ ትምህርት ቤት የመግቢያውን ሁኔታ ተስማምቶበት ወስኖ ከሆነ፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ለሙሉ ኮርስ ከሚከፈለው የትምህርት ክፍያ ያነሰ ምጥጥን/prorated ሊደረግ ይችላል። ምጥጥን የሚደረግበት የጊዜ ሰሌዳ እንደሚከተለው ይሆናል፦

   a) ለአንድ ኮርስ — 25 ከመቶ ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   b) ለሁለት ኮርሶች — 50 ከመቶ ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   c) ለሶስት ኮርሶች — 75 ከመቶ ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

   d) ለአራት ኮርሶች ወይም ከዚያ በላይ —100 ከመቶ ዓመታዊ የትምህርት ክፍያ

4. ከዚህ በላይ III.H.1 ወይም III.H.3. ውስጥ ባሉት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ተማሪዎች ከትምህርት ቤት የለቀቁበት ቀን ምንም ይሁን ምን ተማሪው(ዋ) የተማረ(ች)በት ሴሚስተር ክፍያ ተመላሽ አይደረግም ወይም ተቀናሽ አይታሰብለ(ላ)ትም።

I. የትምህርት ክፍያን መሰብሰብ

ከዚህ ቀጥሎ ያሉት ቅጾች ከቀረቡ በኋላ፦ MCPS ቅጽ 335-73፣Determination of Residency and Tuition Status፣ እና MCPS ቅጽ 335-73A፣ Request to Enroll Nonresident Tuition-paying Student ፡የትምህርት ክፍያ ያልተከፈለ መሆኑን እና የትምህርት ቤት ምደባው የፀደቀ ከሆነ፣ ተቆጣጣሪ ሠራተኛ—

1. በቦርዱ ተቀባይነት ባለው ተመን ላይ በመመስረት ተገቢውን የትምህርት ክፍያ መጠን ይወስናል፣

2. MCPS ቅጽ 335-73A ን/ክፍል III፣ *ነዋሪ ያልሆነ(ች) ተማሪን በትምህርት ክፍያ የማስመዝገብ ጥያቄ፣* መሞላቱን ያረጋግጣል።

3. የክፍያ ሠነድ ለወላጅ/ሞግዚት/ለብቁ ተማሪ ይሰጣል

4. የትምህርት ክፍያውን ይሰበስባል፣ እና

5. የትምህርቱ ክፍያ የፋይናንስ ሂሳቦችን ከ IAE መዛግብት ጋር በየጊዜው በማመሳከር ያረጋግጣል፣

6. ክፍያው መከፈል ከነበረበት ቀን ጀምሮ 30 ቀናት ውስጥ ካልተከፈለ—

    a) ባልተከፈለው ሂሣብ መጠን ወለድ ማስላት ይጀመራል፣

    b) ክፍያ ላልፈጸሙ ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ወለድ የተጨመረበት መሆኑን፣ ያልተከፈለ ገንዘብ ለሚሰበስብ ኤጀንሲ፣ እና/ወይም ከክፍል የመባረር ሁኔታ ሊከተል እንደሚችል ማሳወቅ፣ እና

    c) ለትምህርት ቤቱ እና IAE የነዋሪነት ባለሙያ ያሳውቃል።

IV. *የትምህርት ክፍያ መስፈርቶችን ስለመሠረዝ*

A. MCPS ደንብ JEA-RB ላይ ባለው ድንጋጌ *መሠረት፣ የተማሪዎች ምዝገባ/አድሚሽ*(ዋ) ከ18 ዓመት በታች የሆነ እና በፍርድ ቤት ውሳኔ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ከሆነ(ች) ሞግዚት፣ ወይም ሌላ አዋቂ ሰው፣ ይፋዊ ለሆነ የዝምድና ግንኙነት ሁኔታዎች ብቁ የማያደርጉ፣ እና ወላጆች/ሞግዚቶች በሞንትጎመሪ ካውንቲ መደበኛ ነዋሪ ያልሆኑ ለማስመዝገብ የሚፈልጉ፣ የትምህርት ቤት ባልደረቦች ክፍያን የመሠረዝ ውሳኔ ለመስጠት የሚመለከተውን "IAE" ማማከር ያስፈልጋል።

B. IAE ነዋሪ ላልሆነ(ች) ተማሪ የትምህርት ክፍያ መመዘኛ ማስቀረትን በተመለከተ በተወሰኑ ሁኔታዎች ምክንያት ማቋረጥን የሚያረጋግጥ አስቸጋሪ ሁኔታ/ቀውስ መኖሩን ማረጋገጫ ሰነዶች በሚቀርቡበት ጊዜ በግለሰብ ተማሪ ሁኔታ ላይ ተሞርኩዞ ውሳኔ ይሰጣል። IAE ያደረጋቸው ውሳኔዎች በዓመት ወይም እንደ አስፈላጊነቱ እንደገና ሊገመገሙ ይችላሉ።

C. የትምህርት ክፍያን ለማቋረጥ ብቁ የሚያደርጉ ችግሮች/የቀውስ ሁኔታ ምክንያት ከባድ የቤተሰብ ችግር ሲያጋጥም ነው – ይኼውም፦

1. የወላጅ/የአሳዳጊ መሞት፣ በሞት የምስክር ወረቀት ወይም በሌላ ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ፤

2. ወላጅ/ሞግዚት በጽኑ ህመም ላይ መሆን፣ በኃኪም ማስረጃ የተረጋገጠ ከሆነ፣

3. የወላጅ/አሳዳጊ የአደንዛዥ ዕፅ ሱሰኝነት፣ ከሕክምና ባለሙያ በተሰጠ ደብዳቤ ወይም በሌላ ማስረጃ ከተረጋገጠ፣

4. ወላጅ/ሞግዚት በእስር ቤት መኖራቸውን ከሚመለከተው ህጋዊ አካል፣ ከእስር ቤት፣ ወይም ሌላ የጽሑፍ ማረጋገጫ፣

5. የወላጅ/ሞግዚት ለወታደራዊ ግዳጅ የተመደቡ ከሆነ፣ በወታደራዊ ተቋም ወይም በሌላ ሠነድ ከተረጋገጠ፣ ወይም

6. ያልተለመዱ እና በእርግጠኝነት የተማሪ የመማር ፍላጎቶችን ወይም ጤንነትን የሚቀንሱ/ተፅእኖ የሚያሳድሩ/ ሁኔታዎች፣ በጽሑፉ በግልጽ የሚረጋገጥ እና ተማሪን ካልተለመደ እና ከሚያባብሱ ሁኔታዎች ጋር በማገናኘት የመኖሪያ ቦታ ማዘጋጀት አስፈላጊ የሚሆንበትን ሁኔታ።

D. ተማሪ አብሯቸው ያለ(ች) ነዋሪ የትምህርት ክፍያ መስፈርቶች እንዲሠረዙለ(ላ)ት ለመጠየቅ የሚከተለውን ማቅረብ አለበ(ባ)ት –

1. በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህጋዊ/መደበኛ ነዋሪነት ማረጋገጫ፣

2. ቀውሱን የሚያረጋግጥ እና የተማሪን ሃላፊነት ለነዋሪው የሚያስተላልፍ በወላጅ/በአሳዳጊ የተፈረመ በሠነድ ማረጋገጫ ማህተምና ፊርማ ያለው ደብዳቤ፣

3. ችግሩን የሚያረጋግጡ ሰነዶች፣

4. ስለ ተማሪው(ዋ) ኃላፊነት ከሚቀበል/ከምትቀበል ነዋሪ የተፈረመበት እና ኖቶራይዝ የተደረገበት ደብዳቤ፣ እና/ወይም

5. በፍርድ ቤት የተመደበ(ች) የሞግዚትነት ዶኩመንቶች፣ አግባብነት ካለው

E. አሳማኝ በሆነ ቀውስ ምክንያት የትምህርት ክፍያ መስፈርቶችን መተውን በተመለከተ ውሳኔዎች የሚደረጉት የተጠናቀቁ ሰነዶች በደረሱ 10 የስራ ቀናት ውስጥ ነው። ሁኔታዎቹ በተለይ ውስብስብ ከሆኑ፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች በማሳወቅ የጊዜ ሰሌዳው ሊራዘም ይችላል።

V. *ይግባኝ መጠየቂያ ሥርአት/ሂደት*

A. አንድ ወላጅ/አሳዳጊ ወይም ብቁ የሆነ(ች) ተማሪ IAE ዳይሬክተሩ ውሳኔ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ደንብ ወይም ህግጋት ጋር ይቃረናል ወይም በሚፈለገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ምንም አይነት እርምጃ ካልተወሰደ፣ውሳኔው በተሰጠ 15 ቀናት ውስጥ የፍትህ እና ድርጅታዊ ልማት ክፍልን በማነጋገር ለትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

B. በተለይም ትምህርት ቤት ተጀምሮ ከሆነ እና ተማሪው(ዋ) ትምህርት ለመከታተል በመጠበቅ እንዳይዘገይ IAE፣እንደአግባቡ የይግባኙ ውሳኔውን በማፋጠን ይረዳል።

C. ወላጅ(ወላጆች)/አሳዳጊ(ዎች) በይግባኝ ሂደት ላይ ተማሪው(ዋ) ክፍል እንዲከታተል/እንድትከታተል ከፈለጉ፣ ከአመታዊ ክፍያ 10 በመቶውን እንዲከፍሉ ሊጠየቁ ይችላሉ። የመጀመሪያው ውሳኔ ከተለወጠ ወይም ከተሻሻለ የትምህርት ክፍያው/Tuition በሙሉ ወይም በከፊል ተመላሽ ይደረጋል።

***ስለ ደንቡ ታሪክ፦*** የቀድሞ ደንብ ቁጥር 560-1 ፌብሩዋሪ 26, 1981 ተሻሽሎ ሁለት ሁለት ቦታ ተከፍሏል (ይሄኛው እና JEA-RC) ኦገስት 26 ቀን 1987 ክለሳ ተደርጓል፣ ኦክቶበር 12 ቀን 1992 ክለሳ ተደርጎበታል። ጁላይ 6 ቀን 2001 ክለሳ ተደርጎበታል፣ ማርች 8 ቀን 2005 ክለሳ ተደርጓል፣ ጁላይ 15, 2013 ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ የቀድሞው MCPS ደንብ JED-RA፣ ከተሻሻለ በኋላ MCPS ደንብ JEA-RE *በትምህርት ክፍያ ላይ የተመሰረተ ምዝገባጋር* እንዲዋሃድ ተደርጓል። ኤፕሪል 3, 2019 ክለሳ ተደርጎበታል፣ ጁን 27, 2025 ተሻሽሏል፣ ከጁላይ 1, 2025 ጀምሮ ባለው ይዘት መረጃ ላይ ቴክኒካዊ ማሻሻያዎች ተደርገዋል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል" ። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

በሜሪላንድ ስቴት የሚገኙ የህዝብ ትምህርት ቤቶች እና የህዝብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ት/ቤቶች በሙሉ የሚከተሉትን ህጎች በማክበር እንዲሠሩ የስቴቱ ፖሊሲ/ድንጋጌ ነው፡-

(1)የፌደራል ታይትል VI የዜኘት መብቶች ደንብ 1964፣ እና

(2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-

- (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
- (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
- (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

የግንኙነት መርጃዎች እና የፌደራል፣ የስቴት፣ ወይ የአካባቢ መስፈርቶች በተለያዩ ሕትመቶች መካከል ልዩነት ሊኖራቸው ስለሚችል በዚህኛው ህትመት ላይ የተካተተው የሚፀና መሆኑን ልብ ይበሉ። ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘት እባክዎን ይህን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination.

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | MCPS ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ *** |
|---|---|
| Director of Student Conduct and Appeals<br>Division of Equity and Organizational Development<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator ሰክሽን 504 አስተባባሪ<br>Division of Specialized Support Services, Department of School Counseling<br>850 Hungerford Drive, Room 170, Rockville, MD 20850<br>240-987-8031 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Division of Human Resources and Talent Management<br>Department of Compliance and Investigations<br>15 West Gude Drive, Suite B400, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ*** | |
| Title IX Coordinator<br>Division of Equity and Organizational Development, Department of Student Conduct and Appeals<br>850 Hungerford Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ ማሳወቂያ የተሻሻለውን የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ ማሳወቂያ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር ይጣለጣል።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል። U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), 61 Forsyth St. S.W., Suite 19T10, Atlanta, GA 30303, 404-974-9406 and TDD: 800-877-8339, OCR.Atlanta@ed.gov, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ"Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ኦክቶበር 2025